# የልጅ ማሳደግ ፈቃድ ድንጋጌ

*-በኮሎምብያ ዲስትሪክት መብትዎን ይወቁ-*

## ልጅ ለማሳደግ የሚወሰድ ፈቃድ

የኮሎምብያ ዲስትሪክት የልጅ ማሳደግ ፈቃድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ትምህርት ቤት ነክ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ለመካፈል በ12 ወሮች ውስጥ የ24 ሰዓቶች ፈቃድ (በክፍያ ወይም ያለክፍያ) ይፈቅዳል፡፡ የትምህርት ቤት ዝግጅቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፣ የወላጅ እና አስተማሪ ስብሰባዎች፣ ኮንሰርቶች፣ ቲያትሮች፣ ልምምዶች፣ የስፖርት ዝግጅቶች፣ እና ሌሎች ልጁ/ቷ ተመልካች የሆኑባቸው ሳይሆን የሚሳተፉባቸው ዝግጅቶች፡፡

የትምህርት ቤት ዝግጅቱ ያልተጠበቀ ካልሆነ በስተቀር ሠራተኛው ፈቃዱን ከመጠየቁ ከ10 ቀኖች በፊት ለቀጣሪው ማስታወቅ አለበት፡፡ ፈቃዱ በክፍያ ወይም አለክፍያ፣ የቤተሰብ፣ የዕረፍት፣ የግል ወይም የካሳ ሊሆን ይችላል፡፡

ፈቃድ መስጠቱ የቀጣሪውን ሥራ የሚያጨናግፍ ከሆነ እና የሥራ ውጤቱን ወይም አገልግሎቱን የሚያስቸግር ከሆነ ቀጣሪው ፈቃዱን ሊከለክል ይችላል፡፡

## የወላጅ እና አሳዳጊ ትርጉም

አንድ ሠራተኛ በዚህ ድንጋጌ መሠረት እንደ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ሊቆጠር የሚችለው የሚከተሉት ከሆኑ ነው፣

- የልጁ/ቷ ወላጅ እናት ወይም አባት፣
- የልጁ/ቷ ህጋዊ ባለአደራ፣
- የልጁ/ቷ አሳዳጊ፣
- የልጁ/ቷ አክስት፣ አጎት፣ ወይም አያት፣ ወይም
- ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የተጋባ ወይም በአንድነት የሚኖሩ፡፡

## የቀጣሪ ማስታወቅያ መለጠፍ አስፈላጊነት

ቀጣሪዎ በዚህ ደንብ ስር ትክክል ባልሆነ መንገድ የአሳዳጊ ፈቃድ ከልክሎኛል ብለው ካመኑ ከተፈጸመበት ቀን ጀምረው በአንድ ዓመት ውስጥ ለሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (OHR) አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ አቤቱታ ለማቅረብ፣

### የጥሰት አቤቱታ ማስገባት

ስለ እነዚህ ህጎች ጥሰት አቤቱታ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ አቤቱታ ለማቅረብ፣

- በኦንላይን በ ohr.dc.gov; ወይም
- በአካል - 441 4th Street NW, Suite 570N, Washington, DC 20001.

በተጨማሪም ጥያቄዎች በስልክ ቁጥር (202) 727-4559 ሊመለሱ ይቻላል፡፡